ዜና ዘርሽ

ሰኔ፣ ፪፻፲፭ ዓ.ም



አውታር፡ ችግር የወለደው መፍትሔ

#ናፍቆት
ጎፈሬ አፍሮ ቢት ኮንሰርት

#ግንቦት
ቴስት ኦፍ አዲስ


#ዓለም
የአፍሪካ ባለውለታ



Film

ADVERTISEMENT

TV SHOW



BIRGANA
FILM PRODUCTION

mob: +251 922 995 599

Birgana Film Production


Bole Medhanialem in-front of
sheger house vanquish building
1st floor

Birgana Film

በዚህ እትማችን

ሰኔ ወር ፣ 2011 ዓ.ም.





6-10 #ልዩ ዳሰሳ
አውታር፡
ችግር የወለደው መፍትሔ

17 #ናፍቆት
ጎፈሬ አፍሮ ቢት ኮንሰርት

13-15 #ግንቦት
ቴስት ኦፍ አዲስ
የአዲስ አበባ ጣዕም ልኬት









18-21 #ዓለም **የአፍሪካ ባለውለታ** የአፍሪካ ዋንጫ

ዙር ሠላሳ
በዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ ኃላ. የተ. የግል ማኅበር የምትዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት ናት።
ጎዳር፣ 2011 ዓ.ም ተመሰረተ

ያግኙን
+251 924 312 097
info@dasesaaddis.com
ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310

በመስመር ላይ (Online)
@AccessAddis
@AccessAddis

ውድ የመጽሔታችን ተከታታዮች፣ በቅድሚያ ይህች የሰኔ ወር እትማችን መለቀቅ ከነበረባት ቀን አንድ ሳምንት በመዘግየቷ ከልብ የመነጨ ይቅርታችንን እንድትቀበሉን እንለምናለን።

ባለፈው ሳምንት ሃገራችን ላይ በደረሱት አሳዛኝ ጉዳቶች ከዚያም ጋር ተያያዘ በተፈጠረው ሃገር አቀፍ የአውታረ መረብ ግንኙነት መቋረጥ የተነሳ ልናገኛችሁ አልቻልንም።

በድጋሜ ስለመዘግየታችን ይቅርታ እየጠየቅን

በሃገር መከላከያ ሠራዊት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የነበሩት **ጄኔራል ሰዓረ መኮንን**

በቀደሙት ዓመታት በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በተለያዩ ኃላፊነቶች ሲያገለግሉ የቆዩት ሜጀር **ጄኔራል ገዛኢ ኣብርሃ**

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር የነበሩት **ዶ/ር አምባቸው መኮንን**

በክልሉ የርዕሰ መስተዳደሩ የአደረጃጀት አማካሪ የነበሩት **አቶ እዘዝ ዋሴ**

እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የነበሩት **አቶ ምግባሩ ከበደ**

ላይ የደረሰው ህልፈት እጅግ ያሳዘነን መሆኑና ለቤተሰቦቻቸው፣ ለቅርብ ወዳጆቻቸው እንዲሁም ለመላው ኢትዮጵያውያን ፈጣሪ መጽናናቱን እንዲሰጥ እንለምናለን።

ዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

የዋና አዘጋጁ መልዕክት

ጤና ይስጥልኝ! የዚህች እትማችን ዝግጅት ተጠናቅቆ እንደተለመደው በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ገጾቻችን ለመልቀቅ የመጨረሻ ዝግጅታችንን በማጠናቅቅና ሰዓታችንን በመጠበቅ ላይ ሳለን አስድንጋጭ መረጃዎችን መስማት ጀመረን። የአንድ ሃገር ልጆች አንዱ በአንዱ ላይ በጭካኔ እጅ ማንሳታቸውን ስንመለከት ከባድ ልባዊ ሃዘን ተሰምቶናል።

በኢትዮጵያዊ ባህላችንና ሥርአታችንም መሰረት በሃዘን ወቅት መደሰት የሚገባ ባለመሆኑ ወዲያውኑ የማዘግየት ውሳኔ ላይ ደረስን። ከዚያም በኋላ የነበረው የኢንተርኔት ግንኙነት መቋረጥ ለተከታዮቻችን የሚደርስበትን ልክ የሚገድብ ቢሆንም ለወሩ የተዘጋጀውን መሰናዶ ግን እንድታነቡት መጋበዙ አስፈላጊ መስሎ ስለታየን ከቀረ የዘገየ ይሻላል ብለን ይኸው አድርሰናል።

የዙር ሠላሳ ዝግጅት ክፍል ላለፉት የሃገር መከላከያ ሰራዊት አመራሮችና የአማራ ክልላዊ መንግስት የስራ ኃላፊዎች እረፍተ ነፍስን ለወዳጅ ዘመዶቻቸውም መጽናናትን ፈጣሪ እንዲያድላቸው ተመኝተናል።

መልካም ንባብ!

ዋና አዘጋጅ
ፍጹም ዓለማየሁ
fitsum@dasesaaddis.com


አዘጋጅ
ኢሳያስ ሸፈራው
esayas@dasesaaddis.com


የገበያ ዳይሬክተር
ቴዎድሮስ ብርሃኑ
tewodros@dasesaaddis.com



LEXO
LEXO ENTERTAINMENT
PRESENTS
RAYVANNY | DIAMOND
PLATNUMZ
21 &OVER
ID Required
MEDIA PARTNER
kana
POSTPONED
GOFERE
BEATS FESTIVAL
TICKETS AVAILABLE
RUSCO
VILLAGE
+251 93 793 7653
gofereafrobeatsfestival
MILLIENIUM HALL
ADDIS ABABA
SATURDAY
JUNE
29th
CLASS OF 2019 200
EARLY BIRD 300
DOOR 500
VIP 800
Ethiopian
RUSCO
ZOMA HAIR
ONLINE
ABC

#ልዩ ዳሰሳ

አውታር፡ ችግር የወለደው መፍትሔ









የኢትዮጵያን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ከሚፈታተኑ በርካታ ነገሮች መካከል አንዱ ቴክኖሎጂ ነው። በመጀመሪያ በሸክላ ይደመጥ የነበረው ሙዚቃ ወደ ካሴት ከዚያም ወደ ሲዲ ፈቅ እያለም በሶፍት ኮፒ መሸጥ ጀመረ። ሁላችንም የእጅ ስልኮቻችን የተለያዩ ነገሮችን እንድይዝ ተደርገው ሲሰሩ ለስልክ ተጠቃሚው ህይወቱን ሲያቀልለት ለኢትዮጵያ ሙዚቀኞችና የሲዲ አሳታሚ ድርጅቶች እንቅልፍ የሚነሳ ችግር ሆኖ ተገኝ። ቴክኖሎጂ እንደዚህ ሳያድግ በፊት በኛ አገር ሙዚቀኞች ሥራቸውን ይሠሩና መርካቶ ላሉ አሳታሚዎች በመስጠት ይሸጣሉ። አሳታሚው ካሳተመ በኋላ ደግሞ በመላው አገሪቱ በማሰራጨት ሽያጭ ይካሄድ ነበር። ዓመት ዓመትን ሲወልድ አሠራሩ እየተቀየረ መጥትቷል። ሲዲ የሚያሳትመውም ቁጥሩቀንሷል። ላሳትም ብሎ ደፍሮ ሥራውን ለገበያ የሚያቀርብ ባለሙያም ፈተናው ብዙ ነው። በቀላሉ ኮፒ ተደርገው የሚሸጡበት በመሆኑ ከአጠቃላይ ከሸያጩ እጠቀማለሁ ማለት አይችልም። በዚህ ምክንያት በፊት የነበሩት አሳታሚ ድርጅቶች ከገበያው በመውጣታቸው በዚህ ጊዜ አሳታሚ ድርጅት ማግኝት አዳጋች ያደርገዋል። በርካታ ሙዚቀኞች የሙዚቃ ስራዎቻቸው አልቆ በእነዚህ ተግዳሮቶች ምክንያት ስራዎቻቸውን ለህዝብ ሳያደርሱ ታቀፈውት የተቀመጡ እንዳሉ ይነገራል። አሁን ያለው ድምፃዊ አንድ ነጠላ ዜማ ካወጣ በኋላ ለዩቲዩብ ገጾች ባለቤቶች በመሸጥ፣ ስራው ከተወደደለት ኮንሰርቶች በመስራት ሲቀናም ከሀገር ውጪ እየተጋበዘ ይሰራል። በተለየም በዩቲዩብ ገጾች ባለቤቶች ለአንድ ነጠላ ዜማ ብቻ ከሚከፍሉት የተጋነነ ብር



ጋር ተያይዞ ከሲዲ ሽያጭ አተርፋለሁ የሚል ድምፃዊ እንዳይኖር አድርጓል።

የሙዚቃ አቀናባሪው ኤልያስ መልካ፣ ድምጻዊ ጆኒ ራጋ፣ ድምጻዊ ሃይሌ ሩት፣ የሙዚቀኞች ማኅበር ፕሬዝዳንቱ ዳዊት ይህን ስጋት ይቀረፍ ዘንድመፍትሔ ይሆናል ብለው የሚያቡትን ከአምስት ዓመት በፊት የሙዚቃ ባለሙያዎች በመሰብሰብ ሃሳብ ያወቱና ያወርዱ ጀመር። ከዚያም የሙዚቃ መግዛ መተግበሪያ በመስራት ሙዚቃን በድህረ ገጽ ለመሰጥ ውጥን ይይዛሉ። ይህ ሀሳብ ግን ትልቅ ፈተና ከፊቱ ይጋረጥበታል። ሰዎች ሙዚቃውን መግዛት ቢፈልጉ በምን ሥርዓት መክፈል እንደሚችሉ አይታወቅም። ምክንያቱ ደግሞ የባንክ የክፍያ ስርዓትን በኦን ላየን ግብይት ማድረግ ስለማያስችል ነው። ስለዚህ ያለው አማራጭ ቴሌ ብቻ ነው። በቴሌ በኩል በስልክ ላይ ገንዘብ በመቁረጥ ወይንም የሞባይል ካርድን በመጠቀም ግዢው እንዲፈጸም የሚያደርግ መተግበሪያ ይፋ ለማድረግ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ስምምነት ይፈፀማሉ። እነዚህ ሙዚቀኞች ሥራውን ለመሥራት ከቴሌ ጋር Value Added Service (VAS) ለመሥራት ፈቃድ ማውጣት ያስፈልግ ስለነበር የንግድ ፈቃድ ማውጣት ግዴታ በመሆኑ በዚህ ምክንያት አውታር መልቲ ሚዲያን አቋቋሙ። ድርጅቱ ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በጋራ መሥራት የቫስ (VAS) ፈቃድን ማውጣት ችለዋል። አዲሱ መተግበሪያ ኢትዮጵያውያን የፈለጉትን ሙዚቃ በፈለጉት ጊዜና ቦታ በእጅ ስልኮቻቸው በኢንተርኔት አማካይነት ለመግዛት ያስችላቸዋል። አውታር መልቲ ሚዲያ የተመሰረተው በኤልያስ መልካ፣ ጆኒ ራጋ፣ ዳዊት ንጉሡና ኃይሌ ሩትስ ሲሆን፤ በመተግበሪያው ከሚሸጡት ሙዚቃዎች ኢትዮ ቴሌኮም ድርሻ ይኖረዋል።

ይህ የሙዚቃ መሸጫ መተግበሪያ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የተሠሩ፤ የኢትዮጵያ ሙዚቃዎችን ያቀርባል ተብሏል። በዚሁ የሽያጭ ሥርዓት ድምፃዊ፣ የግጥም ጸሐፊ፣

#ልዩ ዳሰሳ



የሙዚቃ አቀናባሪ፣ የዜማ ደራሲና ፕሮዲውሰር ትርፍ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል። ስለዚህ ከአንድ የሙዚቃ ሥራ ላይ እነዚህ አምስትሥራዎች እያንዳንዳቸው ከሽያጩ ላይ 20 በመቶ ክፍያ ያገኛሉ። በሸክላ የተቀረፁ የድሮ ዘፈኖች፣ በካሴት የተቀዱ የስልሳዎቹና የሰባዎቹ ሥራዎች፣ በሲዲ የነበሩ ሁሉ ተሰብስበው ወደኮምፒውተር የተገለበጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ባለቤቶቻቸው በሕይወት ስለሌሉ ከሕጋዊ ወራሾቻቸው ጋር በመነጋገርና በመፈራረም እንዲጫኑ ይደረጋል። አንድ ድምፃዊ ሥራው አውታር ላይ እንዲጫን፤ ፎርማቱን ወደ ኤም ፒ 3 በመቀየር 224 ኬቢ ወይንም 160 ኬቢ በማድረግ የዘፈኑን ግጥምና ፎቶውን በሶፍት ኮፒ ማስቀመጥ ከዚያ የገዙትን ሰዎችና ምን ያህል እንደተሸጠ ለማወቅ የሚረዳውንኮድ ከማግኘቱ በፊት ከድርጅቱ ጋር መፈራረም ይጠበቅበታል። በተጨማሪም ሙዚቃው በአውታር መተግበሪያ ተጭኖ እንዲሸጥ አምስቱ ባለሙያዎች ተስማምተው መፈረም ይኖርባቸዋል። መተግበሪያው ምስሎች፣ ስለዘፋኙና ሌሎች ሙዚቀኞች መረጃ እንዲሁም የዘፈኑ ግጥም የያዘ ነው።

መተግበሪያው በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ፣ በአማርኛና በእንግሊዘኛ አገልግሎት እንዲሰጥ ሆኖ የተዘጋጀ ከመሆኑ ባለፈ የተለያዩ እምነት ተከታዮችም፤ የሙስሊም፣ የኦርቶዶክስ፣ የፕሮቴስታንት፤ የሚፈልጉትን መንፈሳዊ መዝሙር ወይንም መንዙማ ማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ የተደራጀ ነው። አንድነጠላ ዘፈን አራት ብር ከሀምሳ፤ አምስት ዓመት ያልሞላው ሙሉ አልበም አስራ አምስት ብር ይሸጣል። በአንድ ሲዲ ላይ የሚኖረው ዘፈን ምንም ያህል ቁጥር ቢኖረው ሙሉ አልበም 15 ብር ይሸጣል። ስማርት ስልክ ያላቸው ማስፈንጠሪያውን ሲጫኑ ወዲያውኑ በስልካቸው ላይ መተግበሪያው የሚጫን ሲሆን፤ ስማርት ስልክ የሌላቸው ግን በቁጥር እያስመረጠ እንዲጠቀሙ የሚያስችለው ዩ ኤስ ኤስ ዲ የሚባለው ቴክኖሎጂ ለመጨረስ በሥራ ላይ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል ።







MEMORIES *Beyond Compare*

WEDDINGS • ENGAGEMENTS • MATERNAL • EVENTS

JOHNNY VIDEO
Productions

+251 91 122 1216 | +251 91 277 9977 johnnyvideoproduction
Bole Medhanialem, Berhane Adere Building 2nd floor #204






#ስናላግጥ

ባለፈው ወር ተወዳጅ የነበሩ MEMES

ከ ሀበሻን MEME ጋር በመተባበር

On Instagram
@officialhabeshanmeme

@DAGI







#ግንቦት

ቴስት ኦፍ አጼስ

የአጼስ አበባ ጣዕም ልኬት



#ግንቦት

10

በተለያዩ የአለማችን ሃገራት በተለይ ደግሞ ያደጉት ተብለው በሚጠቀሱት ሃገራት ውስጥ በተለያየ ይዘታና አቀራረብ እንደየ ሃገሩ ባህል እና እሴት ወርሃዊ፣ ሳምንታዊ፣ አመታዊ የሙዝናኛ ዝግጅቶችን ማከናወን የተለመደ ነው። እንደ ጀርመን ያሉ ሃገራት የቢራ ድግስ በማዘጋጀት፣ ዱባይ የተለያዩ የሙዚቃ ድግስ ዝግጅት፣ በዴንማርክ የምግብ ዝግጅት በአለማችን ይታወቃሉ። እንዚህ መሰል የመዝናኛ ዝግጀቶች ከፍተኛ በጀት ተመድቦላቸው የሚካየዱ ሲሆኑ በሐጉራችን አፍሪካም ሆነ በሃገራችን መሰል የመዝናኛ ዝግጅቶች ይካየዳሉ። በሃገራች የተለያዩ የሙዚቃ ዝግጅቶች በተለያየ ቦታና በተለያየ ይዘት ይደራጋል ነገር ግን ይዘቱን ሆነ የዝግጅት አነቱን ወጥ በሆነ መገድ ከአመት አመት ሳይቀየር የሚዘጋጅ የመዝናኛ ዝግጅት ማግኝት አዳጋች ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለየም በመዲናችን አዲስ አበባ ከ 4 አመት በፊት የተጀመረው ቴስ ቶፍ አዲስ የምግብ ና የመጠት የመዝናኛ ዝግጅት ከተማችን ለሚገኝው ነዋሪ በተለይም ወጣት የመዝናኛ አማራጭ እንዲኖረው አድርጓል። ቴስ ኦፍ አዱስ በብሉ ሚዲያ አዘጋጅነት በዋሊያ ቢራ አጋርነት በ 2008 ዓ/ም ነፋሻማ ቦታ በሆነው ትሮፒካል ጋርደን የመጀመሪያ ዝግጅቱን አካየደ። የሳምንቱ የመጨረሻ ሁለት ቀናት ቆይታ ያለው ቴስት ኦፍ አዲስ የተለያዩ የከተማችን የምግብ ሬስቶራንቶች፣ ኬክ ቤቶች፣ በአንድ ጥላ ስር በመሆን የተለያዩ ምግቦችን ለታዳሚያኑ በማቅረብ ከወደ መድረክ ደግሞ የሬጌ አቀንቃኝ የሆነው ጆኒ ራጋ ስራዎችን ለታዳሚያን በማቀንቀን የማይረሳ



#ግንቦት

10

የመጀመሪያ ዝግጅቱን አካሄደ።

ምግቡ፣ መተጠቱ፣ ከወደ መድረክ የሚዘጋጀው በዲጄ በባንድም የሚሰማው የሙዚቃ ዝግጅት ከቦታው ውብ እና ነፋሻማ አየር ጋር ተዳምሮ ቴስ ኦፍ አዲስ ፌቲቫል ተወዳጅ አደረገው። በመንግስት ለልማት የፈለጋል ከተባለበት አሃዱ ብሎ ከጀመረበት ትሮፒካል ጋርደን ወጥቶ ወደ ጎልፍ ክለብ በተዘዋወረበት ሰዓት የመዝናኛ ዝግጅቱ በታዳሚም በአቀራረብም ትንሽ የመቀዛቀዝ አዝሚያማ የታየበት ሲሆን የቦታለውጥ በማድረግ ጊዮን ሆቴል ከአመት በፊት ዝግጅቱን አድርጓል። ቴስስ ኦፍ አዲስ በ 4 ዓመት ቆይታው 18 ጊዜ የመዝኛ ዝግጅቱን ያደረገ ያደረገ ሲሆን ባሳለፍነው ግንቦት ወር የዚህን አመት ሶስተኛ እና የመጨረሻ ዝግጅቱን አካይዷል። እንደተለመደው ሁሉ የከተማችን የሚገኙ ሪስቶራቶች ተሳታፊ በነበረበት ዝግጅት በተለያዩ የከተማችን እውቅ ዲጄዎች በማዋዛት የተዋጣለት ዝግጅቱን አካይዷል። ዘንድሮ በተከያየዱት ሶስቱም ዝግጀቶች የተለያዩ የዳሰሳ አዲስ አባላት ነጻ የመግቢያ ትኬቶችን ከብሉ ሚዲያ ጋር በመተባበር ገብተው እንዲዝናኑ እድሉ ማመቻቸታችን ይታወሳል። ቴስ ኦፍ አዲስ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ ከአዲስ አበባ ወጣ በማለት በረሃዋ ንግስት በሆነችው አዳማ ከተማ ተመሳሳይ የመዝናኛ ዝግጀቱን ለመጀመሪያ ጊዜ አካሂዷል።





ምርትና አገልግሎትዎን በዳሰሳ አዲስ የማህበራዊ ገጾችና በዙር ሠላሳ ላይ ያስተዋውቁ።

በእያንዳንዱ እትም

500,000+

ሰዎች ያዩዎታል

ዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ ታላ. የተ. የግል ማኅበር
+251 924 312 097
marketing@dasesaaddis.com
ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310

#ናፍቆት

ጎፈሬ አፍሮ ቢት ኮንሰርት


አፍሮቢትስ የሙዚቃ የአፍሪካውያን ሙዚቃዎች የሚዘወተር የሙዚቃ ስልት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘት የቻለ የሙዚቃ ስልት ሲሆን ከሌሎች የሙዚቃ ስቶች ጋር በመጣመር የተለየ ድምፅ እና ሪትም በማምጣት በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቷል። በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የአፍሮቢትስ ሙዚቃ አቀንቃኞች በሀገራች በመምጣት የሙዚቃ ስራዎቻቸውን ማቅረብ ችለዋል።

ጎፈሬ አፍሮ ቢት ፌስቲቫል በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙትን በተለይም በምስራቅ አፍሪካ የተለያዩ ባህሎችን እና የቅርፅ አጉልቶ ለማውጣት የታሰበ ፌስቲቫል ሲሆን ጎፈሬ የሚለውን ስያሚ ያገኘው አፍሮ ከሚለው ሌላኛው ስሙ በመወሰድ እንደሆነ የፌስቲቫሉ አዘጋጆች ይገልጻሉ።

የፊታች ቅዳሜ ማለትም ሰኔ 22 በሚሊንየም አዳራሽ ግቢ ውስጥ በሌክሶ ኢንተርቴመንት አዘጋጅነት የወቅቱ የአፍሮቢትስ እውቅ ድምጻዊያን DAIMAOND PALTUNMZ እና **REVANNY** ስራዎቻቸውን ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ድምጻዊ፣ የሙዚቃ ፀሃፊ እና ዳንሰኛ የሆነው NASIBU ABDUL JUMA ወይም በመድረክ ስሙ DAIMAOND PALTUNMZ ታንዛኒያዊ የሙዜቃ አቀንቃኝ ሲሆን እ ኤ አ ከ2009 ጀምሮ ወደ ሙዜቃው ኢንዱስትሪ ተቀላቅሏል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኝት የቻለ የአፍሮቢትስ አቀንቃኝ ነው። ይህ ሙዚቀኛ የተለያዩ በርካታ ሽልማቶችን እጩ በመሆን እና ሽልማቶችን በእጁ አስገብቷል። ከነዚህም ውስጥ በጥቂቱ እንደ MTV MUSIC EUROP AWRAD, MTV AFRICA MUSIC AWRADS, BET AWRADS ሽልማት ከተረከበባቸው ጥቂቶቹ ናቸው። አብሮት ስራዎችን ያቀርባል ተብለው የሚጠበቀው ሌላኛው አቀንቃኝ REVANNY ታዛናዊ ሲሆን ከ DAIMAOND PALTUNMZ በመሆን በርካታ ስራዎችን በጋራ ሰርተዋል።

ከሀገራችን ተወዳጅ ድምጻዊያን መካከል ያሬድ ነጉ፣ ሚኪ ጎንደርኛ፣ ሳንቾ፣ ዊሃ፣ ፀዲ፣ ቲዲ፣ እጊቱ ልቤ ማለ፣ ሶል ሮሚዮ፣ ዜማስ፣ እዮቤድ፣ ቡዜ ማን በቅርቡ በሚደረገው በዚህ የሙዚቃ ድግስ ላይ ስራዎቻቸውን ያቀርባሉ። የመግቢያ ዋጋ ለ2011 ተመራቂ ተማሪዎች 200 ሲሆን ቀድመው ለሚገዙ 300 ብር የኮንሰርቱ እለት 500 ብር እንዲሁም ቪ አይ ፒ 800 ሲሆን ትኬቶቹ ከእፎይ ፒዛ፣ ካራሜል ፔስቲ፣ ቪሌጅ እና ራንጎ በመሸጥ ላይ ይገኛል።



#ዓለም

የአፍሪካ ባለውለታ



#ዓለም

የዛሬ 63 ዓመት በጎርጎሮሳውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ1956 በሊዝበን፣ ፖርቹጋል በተደረገው የዓለም አቀፉ እግር ኳስ ፌዴሬሽን፣ ፊፋ ኮንፍረንስ ላይ አኅጉራዊ የእግር ኳስ ውድድሮችን ለማካሄድ ማቀድ ተጀመረ። ምንም እንኳን አውሮፓውያኑ ይህንን ለማድረግ የማይከብዳቸው የነበረ ቢሆንም አብዛኞቹ አፍሪካውያን ሃገራት ግን በወቅቱ በራሳቸው በአሮፓውያኑ የቅኝ ግዢ ቀንበር ሥር እንደወደቁ ነበር። ይህ መሆኑ ግን ሃገራቱን ከመሰባሰብ ያገደ አልነበረም። እንዲያውም በዚህ ስብስብ ምክንያት ነጻ ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት ላይ የመመካከሪያም መድረክ ሆነ እንጂ።

ግብጽ፣ ሱዳን፣ ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያዎቹ መስራች አባቶች ሆነው በ1957 የመጀመሪያውን የአፍሪካ ዋንጫ ለማድረግ ተሰናዱ፤ ልክ ያኔ የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም ተወለደ። ልክ በአመቱ አራቱ አገራት በካርቱም ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ። ይሁን እንጂ በአፓርታይድ አገዛዝ ትማቅቅ የነበረችው ደቡብ አፍሪካ በሥርዓቱ አስገዳጅነት ነጭ የሆኑ ተጫዋቾች ብቻ ብቻ እንዲሳተፉ በመታቀዱ ከተሳትፎዋ ቀረች በዚህም ምክንያት በግማሽ ፍጻሜ ትገጥማት የነበረችው ኢትዮጵያ ወደ ፍጻሜው በቀጥታ በማለፍ ግብጽን ገጠመች። በማጠቃለያውም ግብጽ በማጨነፏ የመጀመሪያው አፍሪካ ዋንጫ አሸናፊ ሆናለች።

ከሁለት አመታት በኋላም ሁኔታዎች እምብዛም ያልተለወጡላት አፍሪካ በግብጽ አዘጋጅነት እነዚያው ሦስት ሃገራትን አሳትፋ በራሷ በአዘጋጇ ግብጽ አሸናፊነት ተጠናቋል። ከሦስቱ ተሳታፊዎች አዘጋጅነት ያልደረሳት የኛዋ ኢትዮጵያም በ1962 ባዘጋጅበት ወቅት ግን ተሳታፊዎቹም ወደ ዘጠኝ አድጎንገው ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜም ከጥሎ ማለፍ በፊት የማጣሪያ ጨዋታዎች የተደረጉበት 3ኛው የአፍሪካ ዋንጫ አዲስ አበባ ላይ ሲካሄድ



አዘጋጇ ኢትዮጵያ ከግብጽ፣ ናይጄሪያና ቱኒዚያ ጋር ወደ ጥሎ ማለፉ ደርሱ። በቅድሚያ ቱኒዚያን በፍጻሜው ደግሞ ግብጽን በመርታት ኢትዮጵያ ሻምፒዮንነቱን ተረከበች።

ከ1963 በኋላ በጋና አዘጋጅነትና አሸናፊነት የተጀመረው የምዕራፍ አፍሪካ ሃገሮች ከፍተኛ የአሸናፊነት ጉዞ አሁንም ድረስ ቀጥሏል። ይሁን እንጂ በርካታ ዋንጫዎችን በመሰብሰብ ግብጽን የተስተካከላት የለም። እስከ አሁኑ የአፍሪካ ዋንጫ ድረስ ግብጽ ሰባት ዋንጫዎችን ስታሸንፍ ምዕራብ አፍሪካውያኑ ካሜሩን፣ ጋና እና ናይጄሪያ ደግሞ በአምስት፣ በአራትና፣ በሦስት ዋንጫዎች ይከተሏታል። ከ31 የአፍሪካ ዋንጫዎችም ምዕራብ አፍሪካውያኑ 16ቱን ወስደውታል።

በ1996 ከአስርት አመታት እግድ በኋላ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊነቷን ከነአዘጋጅነት ያገኘችው ደቡብ አፍሪካም ከአፓርታይድ ጭቆና በኋላ በ1994 ማጣሪያ ማለፍ ባለመቻሏ ያጣችውን እድል ያገነኘችበት ነበር። በተለይ በዘጠናዎቹ እንደ ጋናዊው አቤዲ ፒሌ የመሳሰሉ ከዋክብት የነገሱባቸው አስደናቂ እና የዓለምን ዐይን ይስቡ የነበሩ ጨዋታዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። የውድድሩም ተሳታፊ ሃገራት ቁጥር ወደ 12 ያደገ ሲሆን በሶስት ቡድን ተከፍለው ይጫወቱ ነበር። በዚሁ አስር ዓመት ውስጥ በደቡብ አፍሪካ በተዘጋጀው 20ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የተሳታፊዎቹ ቁጥር ወደ 16 ያደገ ሲሆን እስከ 2017 31ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ድረስ ቀጥሏል። በዘንድሮው 32ኛው ውድድር ግን ይህ ቁጥር ወደ 24 ከፍ ብሏል።

በርካታ ውጣ ወረዶችን ያሳለፈው ይህ ውድድር በታሪኩ ሦስት አይነት ዋንጫዎችም ነበሩት። የመጀመሪያው ዋንጫ ከብር የተሰራ ነበር። በመጀመሪያው የካፍ ፕሬዚዳንት አብዱላዚዝ ሳሌም ተሰይሞ የነበረው ይህ ዋንጫ በ1978 ጋና በባለቤትነት አሸንፋ የተረከበችው ነው። ሁለተኛው ዋንጃ ደግሞ ከ1980 እስከ 2000 ድረስ ለአሸናፊዎች ሲበርከት የቆየ ሲሆን የአፍሪካ ህብረት ዋንጫ ተብሎ የተሰየመ ሲሆን በክብ ቅርጽ ላይ በተቀረጸ የአፍሪካ ካርታ ላይ የኦሎምፒክ ቀለበቶች የተነቀሱበት ነበር። ይህንን ዋንጫ ለሶስት ጊዜ ዋንጫውን በማሸነፍ ካሜሩን በ2000 ወርሳዋለች። በ2001 ሦስተኛው ዋንጫ ተገለጠ፣ በወርቅ የተለበጠው ይህ ዋንጫ ዲዛይን ተደርጎ የተሰራው በጣሊያን አገር ሲሆን ያለፈው ዋንጫ ባለቤት የሆኑት ካሚሩኖች የአዲሱ ዋንጫ የመጀመሪያ አሸናፊዎችም ነበሩ። በ2010 ላይ ለሦስተኛ ጊዜ ይህንን ዋንጫ ግብጽ ያሸነፈች ቢሆንም ዋናውን ዋንጫ ሳይሆን ልዩ የሆነ የራሱ



#ዓለም

አምሳያ የሆነ ዋንጫ በባለቤትነት እንድታስቀር ተስጥቷታል።

የዘንድሮ አዘጋጅነት ኃላፊነት የተሰጣት የሰባት ጊዜ የዋንጫ አሸናፊ ግብጽም ለአዘጋጅነት የተወዳደረቻትን ደቡብ አፍሪካን ጃንዋሪ 8፣ 2019 መርታቷ ተገልጿል። ከጁላይ 2016 ጀምሮ የዚህ ውድድር ስፖንሰር ለመሆን ለስምንት አመታት የተፈራረመው ቶታል በመሆኑ ዝግጅቱ የቶታል የአፍሪካ ዋንጫ ተሰኝቷል። አሸናፊ ለሆነው ቡድን የ4.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሽልማት የተዘጋጀለት ይህ ውድድር የሽልማት መጠኑ ከምንጊዜውም በላይ ከፍ ያለ ነው ተብሏል።

ስምንት ስታዲዮሞችን ለዚህ ውድድር ዝግጁ ለማድረግ ሽር ጉድ ስትል የቆየቸው ግብጽ ሙሉ ምኞቷ ባይሳካም ፌብሩዋሪ 24/2019 ይፋ እንደተደረገው ስድስቱ ስታዲዮሞቿ ብቻ ለውድድሩ ይውላሉ። እንዲያም ሆኖ ከስድስቱ አንዱ የነበረው በፖርት ሰኢድ የሚገነው አል ማስሪ ክለብ ስቴዲዮሟ በተገኘብት ችግር ምክንያት ካይሮ በሚገኘው አል ሳላም ስታዲዮም እንዲቀየር ተደርጓል። በአራት ከተሞቿ የሚገኙት እነዚህ ስታዲዮሞች ከጁን 21 እስከ ጁላይ 19 ድረስ 24ቱን አገራት ሲያስተናግዱ ይቆያሉ።



የቆይታ አመታት፡ 67 ዓመታት

ተሳታፊ ሃገራት፡ 24

ያለፈውን ዋንጫ አሸናፊ፡ ካሜሩን (በታሪክ ለ5ኛ ጊዜ)

በርካታ ጊዜ አሸናፊ፡ ግብጽ (በጥቅሉ 7 ጊዜ)



CAF Official Link


አማኑኤል
ሀብታሙ
ቤተል
መንግስቴ
ዊንታና
ታደሰ
የኤርሚያስ ታደሰ ፊልም
ዓለም
3ወሪ
እውነቱ እውነት መሆን ብቻ ነው
JE 123 STUDIO & 13 MONTH PICTURE
ተዋናይ ፡ - አማኑኤል ሀብታሙ ፣ ቤቴል መንግስቴ ፣ ዊንታ ታደሰ ፣ ፍቅሩ በቀለ ፣ ደዊት ሙሉጌታ ፣ ያሬድ ኪዳኔ
ረዳት ዳይሬክተር ፡- ፍሬሰላም በቀለ እስክሪን ፕለይ ፡- ኤርሚያስ ታደሰና ፍሬሰላም በቀለ ፕሮዳክሽን ማናጀር ፡- ሔኖክ አስቻለው
ዩኒት ፕሮዳክሽን ማናጀር ፡- ኪሩቤል ሚሊዮን ሜካፕና ኮስቲዩም ፡- ሜሮን ንጉሴ ኮንቲኒቲ፡- ካሊድ አማን ካስቲንግ ፡- 13 MONTH PICTURE
ፕሮዳክሽን ዲዛይነር፡- አቤኔዘር በዙ ፕሮፕስ ፡- መስፍን ማስረሻ ስኮር ፡- ክብረዐብ ጣሰው ዳይሬክተር ኦፍ ፎቶግራፊር፡- ጆሴፍ ኢቦንጎ
ካሜራ፡- ጆሴፍ ኢቦንጎ እና ወሰንሰገድ ንጋቱ ሳዉንድ ፡- ሚካኤል አስፋው ላይት ፡- እዩኤል አያሌዉ ኤዲተር ፡- ሀናኤል ይማም
ፕሮዲዉሰር ፡- ኤርሚያስ ታደሰ ደራሲና ዳይሬክተር፡- ኤርሚያስ ታደሰ
ፖስተር ዲዛይን
B PICTURE



#ፊልሞች

3ተኛው ዓይን

ቆይታ: 1:45
ዘውግ: ልብ አንጠልጣይ
ፀሃፊ: ኤርሚያስ ታደሰ
ዳይሬክተር: ኤርሚያስ ታደሰ
ፕሮዲዩሰር: ኤርሚያስ ታደሰ
ተዋንያን: ቤቴል መንግስቱ፣ አማኑኤል ሀብታሙ፣ ዊንታና ታደሰ፣ ፍቅሩ በቀለ



ወደ ፊት

ቆይታ: 1:45
ዘውግ: አስቂኝ የፍቅር ፊልም
ፀሃፊ: ወንድማገኝ ለማ
ዳይሬክተር: በረከት ወረደ
ፕሮዲዩሰር: ኤልያስ ፋንታሁን
ተዋንያን: ሰለሞን ሙሄ፣ ዕድልወርቅ ጥበቡ፣ እንግዳሰው ሀብቴ፣ ቃልኪዳን ጥበቡ



የሴት ፍቅር

ቆይታ: 1:42
ዘውግ: የፍቅር ፊልም ድራማ
ፀሃፊ: አመሃ ድጉማ
ዳይሬክተር: አመሃ ድጉማ
ፕሮዲዩሰር: ሳምሶን ነጋሽ
ተዋንያን: ባህሬን ከድር (ቤኒ)፣ ሃና መርሃጽድቅ ፣ ኤልያስ አለሙ፣ አለማየሁ በላይነህ፣ ኢሳያስ መለስ